# የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

ሰመጉ

# 143ኛ ልዩ መግለጫ

## በኢትዮጵያ ለብሔረሰብ ተኮር ጥቃቶችና ግጭቶች የማያዳግም የፖሊሲና የአፈጻጸም መፍትሄ ይሰጥ!

**በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በጌዴኦ ዞን በተለያዩ ወረዳዎች እና በሐረሪ ክልላዊ መንግስት በሐረር ከተማ ውስጥ እየተፈፀሙ ያሉ የተለያዩ የመብት ጥሰቶች በአስቸኳይ ይቁሙ!**

ጥቅምት 24 ቀን 2010 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

የምዝገባ ቁጥር 1146

ሰመጉ

**ዋናው ጽ/ቤት፡ አዲስ አበባ**
አ.አ ስታዲየም አጠገብ፣ ላሊበላ ሬስቶራንት ጎን፣ ሣኅለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ፣ ቢ.ሮ ቁጥር 19
ስልክ: (+251) 011 551-7704
ፋክስ: (+251) 011 551-7704
ኢሜይል: info1hrco@gmail.com info@ehrco.org
ድረ ገጽ: www.ehrco.org
ፌስቡክ: https://www.facebook.com/humanrights.council.5?ref=bookmarks
የፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

**የሰብዓዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ መምሪያ**
ስልክ: (+251) 011 558-2387
ኢሜይል: info1hrco@gmail.com /monitoringcomplaints@ehrco.org

**ቀጠና / ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች**

| | |
|---|---|
| ደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ሐዋሳ - ስ.ቁ (+251) 046 220-4500፣ ፖ.ሳ.ቁ 360 |
| ሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ባሕርዳር- ስ.ቁ (+251) 058 220-0240፣ ፖ.ሳ.ቁ 1115 |
| ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ነቀምቴ - ስ.ቁ (+251) 057 660-2664፣ ፖ.ሳ.ቁ 463 |
| ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ድሬደዋ - ስ.ቁ (+251) 025 411 6845፣ ፖ.ሳ.ቁ 2596 |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | አዲስ አበባ ስ.ቁ (+251)011 551-7704፣ ፖ.ሳ.ቁ 2432 |


የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ * Human Rights Council

# ማውጫ


| ተ.ቁ | ይዘቶች | ገጽ |
|---|---|---|
| 1 | የኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ | 1 |
| 2 | የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ | 2 |
| 3 | ብሔረሰቦች ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶችና ግጭቶች በኢትዮጵያ - አጭር ዳሰሳ | 3 |
| 4 | የዚህ ልዩ መግለጫ አስፈላጊነት፣ የምርመራ ሂደትና ዘዴዎች | 8 |
| 4.1 | የልዩ መግለጫው ዋና ዓላማ | 8 |
| 4.2 | ምርመራውና ልዩ መግለጫው የተመሠረተበት የህግ ማዕቀፍ | 8 |
| 4.3 | በምርመራው የተሸፈኑ አካባቢዎችና ምርመራው የተካሄደበት ጊዜ | 8 |
| 4.4 | የመረጃ ምንጮችና የማስረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች | 8 |
| 4.5 | የምርመራ ስራው ውስንነትና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች | 9 |
| 5 | ክፍል አንድ፡ በደቡብ ብሔርብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በጌድኦ ዞን በተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ የተፈፀሙ የተለያዩ የመብት ጥሰቶች | 9 |
| | መግቢያ | 9 |
| 5.1 | በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት (ሕገ ወጥ ግድያ) | 11 |
| 5.2 | የአካል ጉዳት | 14 |
| 5.3 | ንብረት ማውደም | 16 |
| 5.4 | ስለተፈጠረው ችግርና በመንግሥት በኩል ስለተወሰዱት እርምጃዎች ከመንግሥት አካላት የተገኙ መረጃዎች | 41 |
| | ማጠቃለያ | 42 |
| 6 | ክፍል ሁለት፡ በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች | 44 |
| | መግቢያ | 44 |
| 6.1 | የደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች | 44 |
| 6.2 | ማጠቃለያ | 47 |
| 7 | ማሳሰቢያ | 48 |
| | አድራሻዎች | 49 |


## የሰንጠረዦች ማውጫ


ሰንጠረዥ 1፡ አ/ስመት መግለጫ ያወጣባቸው ከብሔር ጥቃትና ግጭቶች ጋር በተያያዘ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ---------- 4

ሰንጠረዥ 2፡ በዚህ ምርመራ የተሸፈኑ ዞኖችና ወረዳዎች ---------- 8

ሰንጠረዥ 3፡ በደቡብ ክልል በጌዴኦ ዞን ተከስቶ በነበረው ጥቃት ህይወታቸውን ያጡ ዜጎች ስም ዝርዝር ---------- 13

ሰንጠረዥ 4፡ ከመስከረም 27-28 ቀን 2009 ዓ.ም በጌዴኦ ዞን በዲላ ከተማና በተለያዩ አካባቢዎች በተፈጠረው ግጭት የቆሰሉ ሰዎች ዝርዝር ---------- 14

ሰንጠረዥ 5፡ በጌዴኦ ዞን በጨለለቅቱ ከተማ የተወሰኑ የጌድኦ ብሔረሰብ ተወላጆች፣ የብሔረሰቡ ተወላጅ ባልሆኑ ዜጎች ላይ የፈፀሙት የንግድና የመኖሪያ ቤት ቃጠሎና ዝርፊያ ዝርዝር ---------- 17

ሰንጠረዥ 6፡ በጌዴኦ ዞን በይርጋጨፌ ከተማ በጌዴኦ ብሔረሰብ ተወላጆች፣ ከጌዴኦ ማኅበረሰብ ውጭ ባሉ ነዋሪዎች ላይ የተፈጸመ የድርጅትና የመኖሪያ ቤት ቃጠሎ ዝርዝር ---------- 21

ሰንጠረዥ 7፡ በጌዴኦ ዞን በይርጋጨፌ ወረዳ በሐሩ ከተማ የጌዴኦ ብሔረሰብ ተወላጆች "ዞናችንን ልቀቁልን" በማለት ከጌዴኦ ማኅበረሰብ ውጭ ባሉ ነዋሪዎች በፈጸሙት ጥቃትና የእሳት ቃጠሎ ሳቢያ የወደሙና የተዘረፉ ንብረቶች ዝርዝርና የዋጋ ግምት ---------- 30

ሰንጠረዥ 8፡ በጌዴኦ ዞን በፍስኃ ገነት ከተማ የጌዴኦ ብሔረሰብ ተወላጅ በሆኑ ሰዎች ከጌዴኦ ማህበረሰብ ውጪ ባሉ ነዋሪዎች ላይ የተፈፀመ የድርጅትና የመኖሪያ ቤቶች ቃጠሎ ዝርዝር ---------- 33

ሰንጠረዥ 9፡ በጌዴኦ ዞን ዲላ ዙሪያ ወረዳ ጪጩ ቀበሌና አካባቢው የጌዴኦ ብሔረሰብ ተወላጅ የሆኑ ሰዎች ባደረሱት ጥቃት ከጌዴኦ ማህበረሰብ ውጪ ባሉ ነዋሪዎች ላይ የተፈፀመ የድርጅትና የመኖሪያ ቤቶች ቃጠሎ ዝርዝር ---------- 38

ሰንጠረዥ 10፡ በጌዴኦ ዞን ዲላ ዙሪያ ወረዳ አንዲዳ ቀበሌና አካባቢው የጌድኦ ብሔረሰብ ተወላጆች "ዞናችንን ልቀቁልን" በማለት በፈጸሙት ጥቃት በቤት እንስሳትና ንብረት ቃጠሎ፣ በዝርፊያ፣ ድብደባ፣ ክብረ ነክ ድርጊትና ድንጋይ ውርወራ ተጎጂ የሆኑ ግለሰቦች ስም ዝርዝርና የጉዳት መጠን---------- 38

ሰንጠረዥ 11፡ በሐረሪ ክልል የአፍረንቀሎ የኦሮሞ ባህልና ታሪክ ማዕከል ለመገንባት የመሰረት ደንጋይ መጣልን ተከትሎ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የተፈጸመባቸው ሰዎች ዝርዝር ---------- 46



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

## 1. ኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ[1]




የመብት ጥሰቱ የተፈጸመባቸው አካባቢዎች

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

[1] ኢትዮጵያ [ካርታ]. <http://www.h2empower.org/aboutus/factsethiopia.html>. (August 11, 2015)

## 2. የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ)፣ የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) በበጎ አድራጎትና ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 መሠረት "ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ማኅበር" ሆኖ በምዝገባ ቁጥር 1146 በሕጋዊነት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅት ነው፡፡ ሰመጉ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብአዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ሲሆን፣ ዓላማውም በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማድረግ ነው፡፡

ዓበይት ዓላማዎቹንና ተልዕኮውን ለማሳካት፣ ሰመጉ ላለፉት 26 ዓመታት ፈርጀ ብዙ የሆኑ የመርሐ ግብር ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፤ በማከናወንም ላይ ይገኛል፡፡ የመንግሥት አካላት በዋነኛነት የግዴታዎች ተሸካሚ፣ ሕዝብም በዋነኛነት የመብቶች ባለቤት እንደመሆናቸው መጠን፣ የመንግሥት አካላትም መብት የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታቸውን በዕውቀት፣ በችሎታና በጽኑ እምነት ላይ ተመርኩዘው እንዲወጡ፣ ሕዝብም እንዲሁ በዕውቀት፣ በችሎታና በጽኑ እምነት ላይ ተመርኩዞ መብቱን እንዲያስከብር ሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም ሰመጉ በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ይሠራል፤ ውጤቶቹን በስብሰባዎችና በልዩ ልዩ የመገናኛ መንገዶች ያሠራጫል፤ የአድቮኬሲ ሥራዎችንም ያከናውናል፤ በነዚህም በፖሊሲዎችና በአፈጻጸማቸው ላይ በጎ ተጽዕኖ ለማሳደር ይጥራል፡፡

የሰመጉ መለያውና ግንባር ቀደም ተግባሩ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝና ሁኔታ መከታተል፣ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ማጣራትና በማስረጃ የተደገፉ መግለጫዎችን ማውጣት ነው፡፡ ሰመጉ በሚያወጣቸው መግለጫዎች ሁሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕና ካሣ እንዲያገኙ፣ የጥሰት ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁና ወንጀል ሠርቶ በነጻ መሄድ እንዲያበቃ፣ ከእያንዳንዱ ክስተት ትምህርት ተወስዶ ለወደፊቱ ጥንቃቄና ተገቢው የፖሊሲና የአፈጻጸም እርማት እንዲደረግ ሲጮህና ሲጠይቅ ቆይቷል፣ አሁንም በመጠየቅ ላይ ነው፤ ለወደፊትም በዚሁ ይቀጥላል፡፡ ከሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ክትትል ተግባራት መካከል፣ ማረሚያ ቤቶችንና የሕግ ታራሚዎችን መጎብኘትና ሰብዓዊ መብቶቻቸው መጠበቃቸውን መከታተል፣ የፍርድ ቤቶችን ሂደት በመከታተል ፍትሐዊነታቸውንና በአጠቃላይም የዳኝነት ነጻነት መኖሩን መከታተል እንዲሁም በመንግሥት የወጡና የሚወጡ ሕጎችን ይዘትና አፈጻጸማቸውን ከሰብዓዊ መብቶች አንጻር መመርመር ይገኙበታል፡፡ ከነዚህ በተጓዳኝ ሰመጉ በተለይ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሰለባ ለሆኑ ዜጎች የተለያየ ደረጃና መልክ ያለው የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

ሰመጉ አሁን በሚገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም ቢሆን፣ ሁኔታና አቅም በፈቀደለት መጠን የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የሕግ የበላይነትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ካለው የጸና ዓላማ አኳያ ተግቶ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

## 3. ብሔረሰቦች ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶችና ግጭቶች በኢትዮጵያ - አጭር ዳሰሳ

ባለፉት 26 ዓመታት በኢትዮጵያ አስከፊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ያስከተሉ በርካታ ብሔር - ተኮር ጥቃቶችና ግጭቶች ተካሂደዋል፡፡ እነዚህ ብሔር - ተኮር ጥቃቶችና ግጭቶች መንስዔዎች እንዲሁም ያደረሱትን ሰብዓዊ፣ ቁሳዊ፣ ስነልቡናዊና ሞራላዊ ጉዳት በትክክል ለማወቅና ለመግለጽ በጣም ሰፊ፣ ጥልቅና ተከታታይ ጥናቶችና ትንተና እንደሚጠይቅ ግልጽ ነው፡፡

የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) ያሁኑ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ) በነዚህ በርካታ ዓመታት ውስጥ ቁጥራቸው የበዛ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የመስክ ምርመራዎችና ጥናቶች 2 ይታወቃል፡፡ እነዚህንም ምርመራዎች ተከትሎ ኢ/ሰመጉ 36 መደበኛ መግለጫዎች፣ 143 ልዩ መግለጫዎች እንዲሁም ቁጥራቸው የበዛ አስቸኳይ ጋዜጣዊ መግለጫዎች አውጥቷል፡፡ መግለጫዎቹም እንደየቅደም ተከተላቸው "የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ"፣"በተወሰነ ቦታና ጊዜ የደረሱ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ጉዳዮችን" እንዲሁም "አጣዳፊ ትኩረትና መፍትሔ የሚሹ አስጊ የመብት ጥሰቶችን" የሚሸፍኑ ናቸው፡፡ ከነዚህም መግለጫዎች መካከል፣ የብሔር ጥቃቶችና ግጭቶችን ተከትለው በዜጎች ላይ የደረሱ ልዩ ልዩ ዓይነት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የሚያሳዩ ከአርባ የሚበልጡ መግለጫዎች ይገኛሉ ፡፡

እነዚህን መግለጫዎች በገለልተኛነትና መፍትሔ በሚሻ አእምሮ ለሚመረምር ዕውነት ፈላጊ ተመልካች፣ የጥቃቶቹን ጊዜና ቦታ፣ ምክንያትና ሽፋኖች፣ የጥቃት ፈጻሚዎችንና የሰለባዎችን ማንነትና ምንነት፣ የሚጠቀሙባቸውን ስልቶችና ዘዴዎች ወዘተ በሚመለከት የነበረውንና ያለውን ተመሣሣይነትና ተደጋጋሚነት ምናልባትም ችግሩ ተባብሶ የታየበትን ሁኔታ፣ የነበሩትን መልኮችና እንዲሁም አሁን የደረሰበትን ደረጃና እያመራ የሚገኝበትን አቅጣጫ ለመረዳት አዳጋች አይሆንበትም፡፡

የዚህ 143ኛ ልዩ መግለጫ ዋና ትኩረት ይህን መሰሉን ትንተና ማድረግ አይደለም፡፡ ይህ ራሱን ችሉ ወደፊት በአፋጣኝ ሊሠራ የሚገባው አንገብጋቢ ሥራ ነው፡፡ ይልቁንም የዚህ አጭር ዳሰሳ ዋና ዓላማ፣ ባላለፉት 26 ዓመታት የከፋ ችግር በማስከተላቸው የተነሳ ኢ/ሰመጉ ተደጋጋሚ ጥያቄ ሲያቀርብባቸው፣ ቅድመ ማስጠንቀቂያና ማሳሰቢያ ሲሰጥባቸው እንዲሁም ያላሰለሰ ጉትጎታ ሲያደርግባቸው የቆዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በመንግሥት በኩል ተገቢው ትኩረት እንዳልተሰጣቸውና በቂ ትምህርትም እንዳልተወሰደባቸው በተጨባጭ ለማመልከት ነው፡፡ ከብሔር ጥቃትና ግጭቶች ጋር በተያያዘ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተገቢ ትኩረት ባለማግኘታቸው ዛሬ የደረሱበትን አስከፊ ደረጃና እያስከተሉት ያለውን እጅግ አሳሳቢ ቀውስና መዘዝ ወደኋላ መለስ ብሎ ባጭሩ በማስታወስ፣ እስካሁንም ከሆነው በላይ እጅግ ሳይዘገይና ከዚህም በላይ ውድ ዋጋ ሳያስከፍሉ መፍትሔ እንዲፈለግላቸው እንደተለመደው ለመጎትጎት ነው፡፡ ከዚህ በታች የሚገኘው ሠንጠረዥ በአጭሩ የሚያሳየው ይህንኑ ነው፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

## ሠንጠረዥ 1፡ ኢ/ሰመጉ መግለጫ ያወጣባቸው ከብሔር ጥቃትና ግጭቶች ጋር በተያያዘ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች

| ተ.ቁ | የመግለጫው ቁጥር | የመግለጫው ርዕስ | መግለጫው የወጣበት ቀንና ዓ.ም | የመግለጫው አጭር ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 1ኛ መደበኛ መግለጫ | የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ 1ኛ መግለጫ | 1984 ዓ.ም | • ሃይማኖትንና ጎሳን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች ምክንያት በምዕራብ ሐረርጌ በሚገኙ የተለያዩ አውራጃዎች በርካታ ሰዎች ተገድለዋል፡፡ |
| 2 | 2ኛ መደበኛ መግለጫ | የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ 2ኛ መግለጫ | የካቲት 5 1984 ዓ.ም | • በተለያዩ ብሔር ተኮር የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል በሚደረገው ፉክክርና ጠብ አጫሪነት ምክንያት በገጠሩ ማህበረሰብ ሕይወት ላይ አደጋ እንዲደርስና የገበሬዎች ንብረትም እንዲወድም ሆኗል፡፡ |
| 3 | 3ኛ መደበኛ መግለጫ | የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ 3ኛ መግለጫ | ሐምሌ 9 1984 ዓ.ም | • በብሔር ንቅናቄ ድርጅቶች ሽኩቻ ሰበብ በአርሲ አስተዳደር በአርባ ጉጉ፣ በመርቲ ደጁ፣ በጎለልቻ ወረዳዎች በርካታ ሰዎች ተገድለዋል፡፡<br>• በአርሲ ነገሌ ወረዳ ቁጥራቸው በርካታ በሆነ የአማራና የከምባታ ብሔረሰቦች ተወላጆች ላይ ግድያ ተፈጽሟል፣ ንብረት ወድሟል፡፡<br>• በመተከል አስተዳደር ከግንቦት ወር 1983 ዓ.ም ጀምሮ በበርካታ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ዜጎች ላይ አሰቃቂ ግድያ ተፈጽሟል፡፡<br>• በበደኖ ከተማ በሰላማዊ ሰዎች ላይ አሰቃቂ ግድያ ተፈጽሟል፡፡<br>• በከፋና በኢሉአባቦር አስተዳደር አካባቢዎች በጉራጌ ማሕበረሰብ አባላት ላይ ከመኖሪያ የማፈናቀል ኢ-ሰብዓዊና ህገ-ወጥ ድርጊት ተፈጽሟል፡፤ |
| 4 | 13ኛ መደበኛ መግለጫ | የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ | ሕዳር 19 1991 | •የጎጂ ኦሮሞዎች ጌዴኦዎች ከሐምሌ 15 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን በሁገረማርያም ወረዳ የጌዴኦና የጎጂ ጎሳዎች አባላት ተሰባጥረው በሚኖሩበት በርካታ የቀበሌ ገበሬ ማህበራት በተከሰተ ግጭት በርካታ የሑለቱም ጎሳዎች አባላት ሞተዋል፣ ተፈናቅለዋል፣ ብዙ ንብረትም ወድሟል፡፡ |
| 5 | 27ኛ ልዩ መግለጫ | በሰሜን ኦሞ ሕዝብ ላይ የተፈጸሙ የመብት ረገጣዎች | ታህሳስ 4 1992 ዓ.ም | • የአሪ፣ የማሊና የወላይታ ህዝቦች የማንነት ጥያቄ በማንሳታቸው ምክንያት፣ በደቡብ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ባለስልጣናት አማካኝነት ግድያ፣ በጥይት ማቁሰል፣ እስራትና ድብደባ ተፈጽሞባቸዋል፡፡ |
| 6 | 29ኛ ልዩ መግለጫ | በሰሜን ኦሞ ሕዝብ ላይ እየቀጠለ ያለው የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ | ጥር 25 ቀን 1992 ዓ.ም | • ከህዝቡ ፍቃድ ውጭ ‹‹ወጋጎዳ›› የተባለ አዲስ ቋንቋ በስራ ላይ እንዲውል መደረጉን ተቃውመው አቤቱታ ባቀረቡ ዜጎች ላይ የመንግስት ታጣቂዎች ግድያና የአካል መጉደል አድርሰዋል፡፡ |
| 7 | 32ኛ ልዩ መግለጫ | አስቸኳይ ትኩረት የሚያሻው የመሬት ይዞታ ጥያቄ | 1992 ዓ.ም | • በሰሜን ሸዋ ዞን በምንጃር ሸንኮራ ወረዳ ልዩ ስሙ ሳማ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ በሚገኙ ነዋሪዎችና አጎራባች በሆነው በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ሸዋ ዞን ቦስት ወረዳ ነዋሪዎች በሆኑ ገበሬዎች መካከል የተፈጠረው የመሬት ይዞታ ይገባናል ጥያቄ ሳቢያ በብዙ አርሶ አደሮች ላይ ብዙ ችግር ፈጥሯል፡፡ |
| 8 | 34ኛ ልዩ መግለጫ | የጎሰኝነት አመራር እያስከተለ ያለው አስከፊ ጥቃት | መስከረም 8 1993 ዓ.ም | • በምስራቅ ወለጋ የተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙ የምክር ቤት አባላት በየአካባቢያቸው የሚኖረውን ህዝብ በማነሳሳት ከአማራ ክልል በመምጣት በአካባቢው እየኖሩ ባሉ አርሶ አደሮች ላይ ከፍተኛ በደል አድርሰዋል፣ በነዚሁ ጠባብ ብሔረተኛ አመራሮች ምክንያት የሰዎች ህይወት ጠፍቷል፣ ሴቶች ተደፍረዋል፣ በርካታ ሰዎች በጥይት ቆስለዋል፣ መኖሪያ ቤቶች ተቃጥለዋል፣ በሺህዎች የሚቆጠሩ ተሰድደዋል፡፡ |
| 9 | 35ኛ ልዩ መግለጫ | እጅግ አሳሳቢና አደገኛ የሆነ የጎሳዎች ግጭት | ጥቅምት 23 1993 ዓ.ም | • በቦረና ዞን በአሬሮ ወረዳ በገሪና በቦረና ጎሳዎች መካከል በተከሰተ የጎሳ ግጭት በርካታ ሰዎች ተገድለዋል፣ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ በንብረት ላይም ውድመት ደርሷል፡፡ |
| 10 | 38ኛ ልዩ መግለጫ | የጎሳና የሀይማኖት ግጭት ያስከተለው ጉዳት | የካቲት 16 1993 ዓ.ም | • በምስራቅ ወለጋ፣ በሐረርና በወለንጪቲ በተከሰቱ የብሔርና የሃይማኖት ግጭቶች ሳቢያ እጅግ በርካታ ሰዎች ተገድለዋል፣ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ ንብረታቸው ወድሟል እንዲሁም ከመኖሪያቸው ተፈናቅለዋል፡፡ |
| 11 | 49ኛ ልዩ መግለጫ | በሸክቾ ዞን በቴፒ ከተማ ከፍተኛ እልቂት ያስከተለ ግጭት | ሚያዚያ 24 1994 ዓ.ም | • በቴፒ ከተማ በሸኮ መዠንገር ህዝቦች የክልል ጥያቄ ምክንያት ከጸጥታ ሀይሎች ጋር በተደረገ ግጭት በርካታ ሰዎች ተገድለዋል፣ ሌሎች በርካቶችም የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ |
| 12 | 51ኛ ልዩ መግለጫ | በአዋሳና አካባቢው በሚገኙ ነዋሪዎች ላይ የደረሰ አስከፊ የመብት ረገጣ | ግንቦት 21 1994 ዓ.ም | • የሲዳማ ዞን መስተዳድር ከአዋሳ ከተማ ወደ አለታ ወንዶ እንዲዛወር ተወስኗል በሚል የሲዳማ ብሔረሰብ አባላት የሆኑ ዜጎች ቅሬታቸውን ለመንግስት በሰላማዊ ሰልፍ ለመግለጽ በመሞከራቸው በመንግስት ታጣቂ ኃይሎች በተወሰደ እርምጃ በርካታ ሰዎች ተገድለዋል፡፡ |
| 13 | 13ኛ መደበኛ መግለጫ | የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ | ህዳር 1991 ዓ.ም | • በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን በሀገረ ማርያም ወረዳ በጌዴኦና በጉጂ ኦሮሞ ብሔረሰቦች መካከል በተከሰተ ግጭት በርካታ ሰዎች ተገድለዋል፣ ተፈናቅለዋል፣ ብዙ ንብረትም ወድሟል፡፡ |
| 14 | 18ኛ መደበኛ መግለጫ | የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ | ነሐሴ 1994 ዓ.ም | • በሰሜን ኦሞ ዞን በጋሞ ጎፋና በደራሼ ልዩ ወረዳ በሚኖሩ የዛይሴና የደራሼ ጎሳዎች መካከል በእርሻ መሬት ይገባኛል ጥያቄ ምክንያት ግጭት ተቀስቅሶ ሰዎች ተገድለዋል፣ የአካ ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ በንብረት ላይም ውድመት ደርሷል፡ |

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

| ተ.ቁ | የመግለጫው ቁጥር | የመግለጫው ርዕስ | መግለጫው የወጣበት ቀንና ዓ.ም | የመግለጫው አጭር ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|
| 15 | 55ኛ ልዩ መግለጫ | በአኝዋክና በኑዌር ጎሳዎች መካከል በተነሳ ግጭት የደረሰ ከፍተኛ እልቂት | ጳጉሜ 1 ቀን 1994 ዓ.ም | • የኑዌር ተወላጅ የነበሩት የጋምቤላ ክልል ም/ፕሬዝዳንት ከሞቱ በኋላ በምትካቸው ሌላ የኑዌር ተወላጅ ሳይሾም በመቅረቱ በጎሳው ተወላጆች ዘንድ የተፈጠረው ‹‹ቦታውን የከለከሉን አኝዋኮች ናቸው›› የሚል ቅሬታ ሲብላላ ቆይቶ በተከሰተ ግጭት በርካቶች ተገድለዋል፣ ከፍተኛ የንብረት ውድመትም ደርሷል፡፡ |
| 16 | 59ኛ ልዩ መግለጫ | አስቸኳይ መፍትሄ የሚያሻው የዲዚና የሱርማ ብሄረሰቦች ግጭት | የካቲት 5 1995 ዓ.ም | • ከብሔር ፖለቲካ ጋር በተያያዘ በቤንች ማጂ ዞን በማጂ፣ በጀባና በሱርማ ወረዳዎች ውስጥ በሚኖሩ የሁለቱ ብሔረሰቦች ተወላጆች መካከል መናናቅ በመፈጠሩ ምክንያት ግጭት ተቀስቅሶ የሰው ህይወት አልፏል፣ ብዙ ሰዎች የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ ግምቱ ከፍተኛ የሆነ ንብረት ወድሟል፡፡ |
| 17 | 66ኛ ልዩ መግለጫ | በቤንች ማጂ ዞን በድጋሜ የተከሰተ የጎሳ ግጭት | ጥቅምት 4 1996 ዓ.ም | • ከሱዳን ድንበር ወደ ጃባና ቱም የተሰደዱ አባላት በዲዚና በሜኒት ጎሳዎች ላይ ጥቃት በማድረሳቸው የሰው ህይወት ጠፍቷል፣ ንብረት ወድሟል፡፡<br>• በሱርማና በአኝዋክ ጎሳዎች መካከል በተቀሰቀሰ የጎሳ ግጭት ምክንያት በርካታ ሰዎች ተገድለዋል፡፡ |
| 18 | 71ኛ ልዩ መግለጫ | በምዕራብ ሐረርጌ ዞን የተከሰተ የጎሳዎች ግጭት | ታህሳስ 20 1996 ዓ.ም | • በምዕራብ ሐረርጌ ዞን የሚገኘው ሚኤሶ ወረዳ ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በኦሮሚያና በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልሎች እንዲተዳደር በመደረጉ በሁለቱ ክልሎች ተወላጆች መካከል የተፈጠረው የይገባኛል ጥያቄ ባስከተለው ግጭት ምክንያት በሰው ህይወት፣ አካልና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል፡፡ |
| 19 | 72ኛ ልዩ መግለጫ | በጋምቤላ ክልል የተፈጸመ ከፍተኛ እልቂት ያስከተለ ጥቃት | ታህሳስ 26 1996 ዓ.ም | • ጎሳን መሰረት አድርጎ የተዘረጋው የአስተዳደር መዋቅር የፈጠረው ቅራኔ፣ ስልጣን የያዘው ጎሳ አባላት የፈጸሙት ግድያ የቀሰቀሰው ቂጣ ለበርካቶች ህይወት ማለፍ ምክንያት ሆኗል፡፡ |
| 20 | 73ኛ ልዩ መግለጫ | በምዕራብ ሐረርጌ ዞን በድጋሜ የተከሰተ የጎሳዎች ግጭት | | • ሚኤሶ ወረዳ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ የሶማሌ ጎሳ ተወላጆች ቦርደዴ ቀበሌ ውስጥ የሚሰበስበው የጫት ቀረጥ ለእኛም ይገባናል በሚል ያነሱትን ጥያቄ ተከትሎ በኦሮሞና በሶማሌ ጎሳዎች መካከል ግጭት ተቀስቅሶ በርካታ ሰዎች ተገድለዋል፣ ቆስለዋል፡፡ |
| 21 | 82ኛ ልዩ መግለጫ | በምስራቅና በምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች ውስጥ የተከሰቱ የጎሳ ግጭቶች | መጋቢት 9 1997 ዓ.ም | • በኦሮሚያና በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልሎች አጎራባች አካባቢዎች ላይ በድንበር ይገባኛል ጥያቄ በተቀሰቀሰ ግጭት በርካታ ሰዎች ተገድለዋል፣ ቆስለዋል፡፡ |
| 22 | 87ኛ ልዩ መግለጫ | አደገኛና አሳሳቢ እየሆነ የመጣው የጎሳዎች ግጭት | ነሓሴ 16 1997 ዓ.ም | • በምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች ውስጥ የኦሮሞና የሶማሌ ብሔሮች በሚያነሱት የድንበር ይገባኛል ጥያቄ ምክንያት በተቀሰቀሰ የብሔር ግጭት በርካቶች ሞተዋል፣ ቆስለዋል፣ ንብረት ወድሟል፡፡<br>• የጉጂና ጎብራ ጎሳዎች ባነሱት የቀበሌ ይገባናል ጥያቄ ምክንያት በተከሰተ ግጭት በርካታ ሰዎች ተገድለዋል፣ ቆስለዋል፡፡ |
| 23 | 91ኛ ልዩ መግለጫ | ዘረኛ ቅስቀሳ ይቁም | ታህሳስ 24 1998 ዓ.ም | • በኦሮሚያ ክል በአርሲ ዞን ኮፈሌ ወረዳ በቆሬ ከተማና አካባቢዋ በዘርና በሃይማት ስም በተከሰተው ግጭት የሰው ህይወት ጠፍቷል፣ ንብረ ት ወድሟል፡፡ |
| 24 | 100ኛ ልዩ መግለጫ | አጥፊዎች ለፍርድ መቅረባቸው በጎ ድርጊት ነው | ሚያዚያ 22 1999 ዓ.ም | • በጌዴኦ ዞን በጎሳ ግጭት ምክንያት ለተፈናቀሉ ዜጎች የመልሶ ማቋቋም ተደርጓል፣ ለአራት ከተሞች የመልሶ ማቋቋም እንዲደረግ ጥሪ ቢቀርብም የመልሶ ማቋቋሙ ስራ ግን አልተሰራም፡፡ |
| 25 | 106ኛ ልዩ መግለጫ | ለጎሳ ግጭቶች ዘላቂ መፍትሄ ይሰጥ | ጥር 22 2000 ዓ.ም | • ነሓሴ 8 ቀን 2008 ዓ.ም በጂማ ዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከብሔር ጋር በተያያዘ በተፈጠረው የተማሪዎች የእርስበእርስ ግጭት በተማሪዎችና በንብረት ላይ ከባድና ቀላል ጉዳት ደርሷል፡፡ |
| 26 | 107ኛ ልዩ መግለጫ | የብሔረሰቦች ራስን የማስተዳደር ጥያቄ ዘላቂ መፍትሄ ያሻዋል | የካቲት 2 200 ዓ.ም | • በደ/ብ/ብ/ህ/ክልል በሚኖሩ የኮይራ ብሄረሰብ አባላትና በአዋሳኙ በኦሮሚያ ክልል በሚኖሩ የጉጂ ብሄረሰብ አባላት መካከል በተከሰተ ግጭት የሰው ህይወት ጠፍቷል፣ የንብረት ውድመት ደርሷል፡፡ |
| 27 | 109ኛ ልዩ መግለጫ | እየተባባሰ የመጣው የጎሳ ግጭት ዘላቂ መፍትሄ ያስፈልገዋል | ሚያዚያ 29 2000 ዓ.ም | • በደ/ብ/ብ/ህ/ክልል ነዋሪ የሆኑ የገዋዳ (አሌ) ብሄረሰብ አባላት ‹‹ልዩ ወረዳ ይሰጠን›› የሚል ጥያቄ በማንሳታቸው ምክንያት ከፌደራል ፖሊስ ጋር በተፈጠረ ግጭት የበርካታ ሰዎች ሕይወት አልፏል፡፡ |
| 28 | 110ኛ ልዩ መግለጫ | እየተባባሰ የመጣው የጎሳ ግጭት ተገቢ ትኩረት ይሰጠው | ሰኔ 3 2000 ዓ.ም | • በኦሮሚያና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልሎች መሀል ባሉ አዋሳኝ ቀበሌዎች ነዋሪዎች በሆኑ የኦሮሞና የጉሙዝ ብሔሮች ተወላጆች መካከል በተቀሰቀሰ ግጭት በርካታ ሰዎች ተገድለዋል፡፡ |
| 29 | 111ኛ ልዩ መግለጫ | ተገቢ ትኩረትና ዘላቂ መፍትሄ ለጎሳ ግጭቶች | መስከረም 29 2001 ዓ.ም | • በጉጂና በቦርጂ ብሄረሰቦች መካከል በድንበርና በውሃ ምንጭ ይገባኛል ጥያቄ ምክንያት የተነሱ ተደጋጋሚ ግጭቶች ለበርካታ ሰዎች ሕይወት ማለፍ ምክንያት ሆነዋል፡፡ |
| 30 | 25ኛ መደበኛ መግለጫ | የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ | ነሓሴ 1998 | • በኦሮሚያ ዞን ጉጂ ዞን አዶላ ወረዳ አዶ ሸኪሶና በቦሬ ወረዳዎች እና በደቡብ ክል በጌዴኦ የተፈጸመ የጎሳ ግጭት፡፡ |

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ • Human Rights Council

| ተ.ቁ | የመግለጫው ቁጥር | የመግለጫው ርዕስ | መግለጫው የወጣበት ቀንና ዓ.ም | የመግለጫው አጭር ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|
| 31 | 27ኛ መደበኛ መግለጫ | የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ | ግንቦት 14 ቀን 1999 ዓ.ም | • በኦሮሚያ ክልል በጂማ ዞን ሰኮሩ ወረዳ የየም ብሔረሰብ ተወላጆች ወደ ደቡብ ክልል እንዲካተቱ ጥያቄ በማንሳታቸው ከኦሮሚያ ክልል ታጣቂዎች ጋር ግጭት ተከስቶ የብዙ ዜጎች ሕይወት ጠፍቷል፣ በብዙዎች ላይም የአካል ጉዳት ደርሷል።<br>• በጌዴኦ ዞን ዲላ ዙሪያ በቱምቲቻ ቀበሌ ሀዴሞና ጎርሳ በተባሉ ጎሳዎች መካከል በተከሰተ ግጭት የሰው ሕይወት ጠፍቷል፣ ንብረት ወድሟል። |
| 32 | 29ኛ መደበኛ መግለጫ | የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ | ጥር 15 ቀን 2000 ዓ.ም | • በደቡብ ክልል በሲዳማ ዞን ወንዶ ገነት ወረዳ ነዋሪዎች የሆኑ የጉጂ ብሔረሰብ አባላት ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ በማንሳታቸው ምክንያት ከሲዳማ ብሔረሰብ አባላት ጋር በመጋጨታቸው የሰው ሕይወት ጠፍቷል፣ የአካል ጉዳት ደርሷል፣ ንብረት ወድሟል። |
| 33 | 30ኛ መደበኛ መግለጫ | የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ | ሚያዚያ 15 2000 ዓ.ም | • በኦሮሚያ ክልል በተልተሌ ወረዳ በቦረና ኦሮሞዎችና በኮንሶ ብሔረሰብ አባላት መካከል በተፈጠረ ግጭት በርካታ ሰዎች ተገድለዋል። |
| 34 | 32ኛ መደበኛ መግለጫ | የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ | ታህሳስ 13 2001 ዓ.ም | • በምዕራብ ሐረርጌ ዞን መኢሶ ወረዳ ‹‹የመንግስት የኃላፊነት ቦታዎች በሐውያ ጎሳ አባላት ብቻ ተይዘዋል›› የሚል ቅሬታ የተፈጠረባቸው የኢሳ ጎሳ አባላት ከሐውያ ጎሳና ከኦሮሞ ብሄረሰብ አባላት ጋር ተጋጭተው የሰው ህይወት ጠፍቷል፣ በርካቶች ቆስለዋል።<br>• በምዕራብ አርሲ ዞን በሻላ ወረዳ በላጆ ቀርጣፋ ቀበሌ ነዋሪዎች የሆኑ የአላባ ብሄረሰብ አባላት በኦሮሚያ ክልል አስተዳደር ስር መካለላቸው ቅሬታ ፈጥሮባቸው በደቡብ ክልል ወደሚገኘው የአላባ ልዩ ወረዳ እንዲካለሉ ጥያቄ በማንሳታቸው በቀበሌና ወረዳ ባለስልጣናት አነሳሽነት ጥቃት ተፈጽሞባቸው የሰው ሕይወት ጠፍቷል። |
| 35 | 144ኛ ልዩ መግለጫ | በደቡብ ክልል ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ በመነሳቱ ምክንያት የደረሰ የመብት ጥሰት | የካቲት 2003 ዓ.ም | • በጉራጌ ዞን ማረቆ ወረዳ የሚኖሩ የኮንቶማ ማህበረሰብ አባላት ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ በማንሳታቸው ድብደባ፣ እስራትና ግድያ ተፈጽሞባቸዋል። |
| 36 | 128ኛ ልዩ መግለጫ | መንግስት ለህዝቦች ጥያቄ በሕግ አግባብ ምላሽ ይስጥ! | 2005 ዓ.ም | • ቢጋሞ ጎፋ ዞን ቁጫ ወረዳ የሚኖሩ የቁጫ ህዝብ ተወካዮች ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ በማቅረባቸው የመንግስት አካላት ዛቻ፣ ድብደባ፣ ሕገ-ወጥ እስራትና የተለያዩ የመብት ጥሰቶች ፈጽመውባቸዋል። |
| 37 | 132ኛ ልዩ መግለጫ | የዜጎች የህይወት፣ የአካል ደህንነት፣ የነጻነትና የመዘዋወር መብት ይከበር! | ጥቅምት 2007 ዓ.ም | • ቢጋምቤላ ክልል በመዠንገር ዞን በተከሰተው የጎሳ ግጭት የብዙ ዜጎች ሕይወት አልፏል። |
| 38 | 117ኛ ልዩ መግለጫ | በተደጋጋሚ እየተከሰቱ ለብዙ ሰዎች ህይወትና ንብረት መጥፋት ምክንያት ለሚሆኑ ግጭቶች ዘላቂ መፍትሄ ይሰጣቸው! | ግንቦት 8 2003 ዓ.ም | • ቢጋሞ ጎፋ ዞን በከንባ ወረዳ በሶርባና በበልታ ቀበሌዎች መካከል ከየካቲት 3 እስከ 7 ቀን 2003 ዓ.ም በተከሰተ ግጭት ከበልታ ቀበሌ 7 ሰዎች፣ ከኮሌ ቀበሌበ 3 ሰዎች እና ከሶርባ ቀበሌ 1 ሰው ተገድሏል፣ ንብረትም ወድሟል። |
| 39 | 118ኛ ልዩ መግለጫ | ዜጎች በሁሉም መብቶች እኩል ተጠቃሚ ይሁኑ! | ታህሳስ 2004 ዓ.ም | • በከፋ ዞን በገዋታ ወረዳ ነዋሪዎች የሆኑ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ልጆቻቸውን በቋንቋቸው ለማስተማር የመብት ጥያቄ በማንሳታቸው በዞኑ ባለስልጣናት እስራት፣ እንግልት፣ ድብደባና የንብረት ውድመት ተፈጽሞባቸዋል። |
| 40 | 139ኛ ልዩ መግለጫ | በዜጎች ላይ የሚፈጸም ሕገ-ወጥ ግድያ በአስቸኳይ ይቁም! | ጥቅምት 23 2008 ዓ.ም | • በሶማሌ ክልል የሚኖሩ የሬርባራና የዱቤ ጎሳዎች የማንነት ጥያቄ በማንሳታቸው የሶማሌ ክልል ልዩ ፖሊስ ኃይል ታህሳስ 1 እና 2 2006 ዓ.ም  በፈጸመው አሰቃቂ የጅምላ ግድያ ከ65 በላይ ሰዎች የተገደሉ ሲሆን ከ153 በላይ ቆስለዋል። |
| 41 | 141ኛ ልዩ መግለጫ | የማንነት ጥያቄ በሚያነሱ ዜጎች ላይ የሚፈጸም ጥቃት በአስቸኳይ ይቁም | ግንቦት 24 2008ዓ.ም | • የወልቃይት፣ ቅማንት፣ኮንቶማ እና ቁጫ ብሄረሰቦች የማንነት ጥያቄ በመጠየቃቸው ምክንያትየተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች። |

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ • Human Rights Council

ከላይ በሚገኘው ሠንጠረዥ ውስጥ በዝርዝር እንደተመለከተው፣ የብሔር ጥቃትና ግጭቶች እንዲሁም አድሏዊ አሰራሮችና በደሎች፣ በጊዜያዊና ለዘለቄታው እንዲቆሙና እንዲቀሩ በፖሊሲም ሆነ በአፈጻጸም ደረጃ ተገቢ ሥራ አልተሠራም።

ለብሔር ጥቃቶችና ግጭቶች በቂ ትኩረት ባለመሰጠቱ፣ ይህንኑ ለመከላከልም አስፈላጊው የህግና ተቋማዊ ስራ ባለመሠራቱ ዛሬ ምን ያህል አስከፊና አስፈሪ ደረጃ ላይ እንንደደረሱና እነርሱን ተከትሎም እየተፈጸመ ያለውን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ለመረዳት የሚያስችሉ በርካታ ማሳያ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። ለምሳሌ ሰመጉ በጳጉሜ 4 ቀን 2009 ዓ.ም. ባወጣው አስቸኳይ ጋዜጣዊ መግለጫ ክፍል ሁለት ላይ፡ "በድንበር ይገባኛል ጥያቄዎች ሰበብ የከፉ ግጭቶች ከመቀስቀሳቸው በፊት መንግስት ከሕብረተሰቡ ጋር በመመካከር አስቸኳይ መፍትሄ ይስጥ" በሚል ርዕስ ውስጥ እንደተመለከተው፣ በአሁኑ ጊዜ በሐገራችን በርካታ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች በርካታ የብሔር ጥቃቶችና ግጭቶች እየተካሄዱ ነው፣ ብሔር ተኮር የሰብዓዊ መብት ረገጣዎችም ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመሩ መጥተዋል። በጳጉሜ 4ቱ የሰመጉ ጋዜጣዊ መግለጫ ከተጠቀሱት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

- በኦሮሚያና በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልሎች መካከል እስካሁን ገና ሙሉ በሙሉ ያልቆመውና አሻራው አሁንም ትኩስ የሆነው ጥቃትና ግጭት፣
- በቤኒሻንጉል ጉሙዝና በኦሮሚያ ክልሎች መካከል (ሰርቦ፣ አባያና ደንቢ)፣ እየደረሰ ያለው ጥቃትና ግጭት፣
- በኦሮሚያ ክልል የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ በሚኖርበት ገላና፣ አባያና የቡሌ ሆራ ወረዳዎች አዋሳኝ አካባቢዎች፣
- በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የኮሬና የቡርጂ ብሄረሰብ በሚኖርበት በአማሮ ወረዳና በቡርጂ ወረዳ፣
- በደቡብ ብሔር ብሐረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በሲዳማ ዞን በቦረቻ ወረዳ በሚገኙ የሲዳማ ብሔረሰብ አባላትና በወላይታ ዞን በምዕራብ አባያ ሁንቦ ወረዳ በሚገኙ የወላይታ ብሔረሰብ አባላት መካከል ያለ ፍጥጫ፣
- ከነዚህም በተጨማሪ እስከ ጥቅምት ወር 2010 ዓ.ም ድረስ በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን በሐገረ ማርያም ከተማ በሚኖሩ ኦሮሞ ያልሆኑ ዜጎች ላይ የደረሰው ማሸማቀቅና እንግልት፣
- በቅርቡ በነቀምት፣ ቡኖ በደሌ፣ቤኒሻንጉል ጉሙዝ የተፈጸሙ ጥቃቶች፣
- በአፋርና በሶማሌ ብሄረሰቦች መካከል የተፈጠረ ግጭት

እነዚህም ጥቃቶችና ግጭቶች "በጊዜ ካልተፈቱ ስፋቱንና መዳረሻውን ለመተንበይ የሚያስቸግር የከፋ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት እንዲሁም የሰላም፣ መረጋጋትና የባሱ የአንድነት ቀውሶችን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ" ሰመጉ ስጋቱን መግለጹ ይታወሳል። ሰመጉ እነዚህን የብሔር ጥቃቶች፣ ግጭቶችና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ በተለይም በኦሮሚያና በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልሎች ውስጥ የደረሰውንና እየደረሰ ያለውን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በዝርዝርና በጥልቀት ለማጣራት የአቅም ውሱንነት ገጥሞት የቆየ ቢሆንም፣ ችግሩ በመፈታቱ በቅርብ ጊዜ የመስክ ምርመራና ጥናት ሥራውን በተሟላ ሁኔታ እንደሚሠራ ለመግለጽ ይወዳል።

ከነዚህ በተጨማሪም የዚህ የ143ኛ ልዩ መግለጫ ዋና ትኩረት የሆኑትና ከአንድ ዓመት በፊት (መስከረም 2009) በደቡብ ክልል በጌዴኦ ዞንና ከጥቂት ወራት በፊት (በሰኔ 2009) በሐረሪ ክልል የደረሱትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፣ እየከፋና በአደገኛ አቅጣጫ በመጓዝ ላይ ለሚገኘው ብሔር ተኮር ጥቃቶችና ግጭቶች እንደማሳያ ሊወሰዱ ይችላሉ።

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

# 4. የልዩ መግለጫው ዓላማ፣ የምርመራ ሂደትና ዘዴዎች

## 4.1 የልዩ መግለጫው ዋና ዓላማ

ቀደም ብሎ ከላይ እንደተመለከተው ሰመጉ በደ/ብ/ብ/ክልል በጌዴኦ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች ውስጥ እንዲሁም በሐረሪ ክልል እና በድሬደዋ ከተማ ውስጥ በመገኘት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ የመስክ ምርመራ አካሄዷል። የዚህ ልዩ መግለጫ አቢይ አላማ ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በበቂ ማስረጃ አስደግፎ በማቅረብ መፍትሄ እንዲሰጣቸው፣ ጥሰቶች እንዲቆሙና ሌሎች የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ የመከላከል እርምጃ እንዲወስድ ለማሳሰብ፣ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ካሳ እንዲሰጣቸውና ድርጊቱን የፈጸሙና ያስፈጸሙ አካላት በህግ እንዲጠየቁ፣ ጥሰት ፈጽሞ ሳይጠየቁ መቅረት እንዲቆምና ተመሳሳይ የመብት ጥሰቶች በድጋሚ የማይፈጸሙበት የፖሊሲና የአሰራር ማስተካከያዎችና እርማቶች ከወዲሁ በተጨባጭ እንዲደረጉ መጠየቅና መጎትጎት ነው።

## 4.2 ምርመራውና ልዩ መግለጫው የተመሠረተበት የህግ ማዕቀፍ

በዚህ ልዩ መግለጫ ውስጥ ይፋ የተደረጉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ዓይነትና ዘርፍ ለመረዳትና ለማሳየት በዋና መሠረትነት የሚያገለግሉት፣ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት፣ የአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብቶች ቻርተር እና ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውና ግዴታም የገባችባቸው የተለያዩ የዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ ናቸው። የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በየዘርፋቸው በተገለጹበት ቦታ ሁሉ እነዚህ የሕግ ማዕቀፎች በመነሻነትና በማመሳከሪያነት ተጠቅሰዋል።

## 4.3 በምርመራው የተሸፈኑ አካባቢዎችና ምርመራው የተካሄደበት ጊዜ

ይህ 143ኛ ልዩ መግለጫ የሚመለከተው በደ/ብ/ብ/ህ/ክልል በጌዴኦ ዞን እና በሐረሪ ክልላዊ መንግስት ውስጥ የተፈጸሙትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ነው። በጌዴኦ ዞን የመብት ጥሰቱ የተፈጸመው ከመስከረም 27-28 ቀን 2009 ዓ.ም ሲሆን ይህንንም የማጣራት ስራ የተሰራው በሁለት ዙሮች ማለትም በህዳርና ነሐሴ 2009 ዓ.ም ነው። እንዲሁም በሐረሪ ክልል ውስጥ የመብት ጥሰቱ የተፈጸመው ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ሲሆን ሰመጉ ባለሙያዎቹን መስክ ልኮ የማጣራት ሥራውን የሰራው ነሐሴ ወር 2009 ዓ.ም. የመጀመሪያው ሳምንት ላይ ነው። ሰመጉ ለዚህ መግለጫ የበቁ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ምርመራ ያካሄደባቸው ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ በዝርዝር ተመልክተዋል።

**ሠንጠረዥ 2፡ በዚህ ምርመራ የተሸፈኑ ዞኖችና ወረዳዎች**

| ተ.ቁ | የክልሉ ስም | ወረዳ/ ከተማ |
|---|---|---|
| 1 | ደቡብ ክልል (ጌዴኦ ዞን) | ይርጋጨፌ፣ ኮቸሬ፣ ዲላ፣ ወናጎ፣ ፍስሀገነት፣ ጨለለቅቱ እና ዙሪያ ቀበሌዎች |
| 2 | ሐረሪ ክልል | ሐረር |
| 3 | ድሬደዋ ከተማ አስተዳደር | ድሬደዋ |

## 4.4 የመረጃ ምንጮችና የማስረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) ይህንን ምርመራ በሚያካሂድበት ወቅት ግኝቶቹን ለማረጋገጥና ለማጠናከር በቀጥታ ከተጎጂዎችና ከተጎጂ ቤተሰቦች አቤቱታና ማስረጃ፣ ከምስክሮች የምስክርነት ቃል፣ ድርጊቱ በተፈፀመባቸው አካባቢዎች በአካል በመገኘት ሁኔታውን በዓይን በማየትና በማጥናት፣ ከአካባቢው ነዋሪዎችም በመረዳት በተጨማሪም የሠነድ፣ የፎቶግራፍና የቪዲዮ ማስረጃዎችን ለመውሰድና ለመሰብሰብ ተችሏል። እንዲሁም በተቻለበት ጊዜ ሁሉ ከመንግስት አካላት መረጃና ማስረጃ ተሰባስቧል።

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

## 4.5 የምርመራ ስራው ውሱንነትና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) አሁን የሚገኝበት በጣም ውሱን የሆነ የሰው ኃይል፣ የገንዘብና የምርመራ ቁሳቁስ አቅም፣ ቀውሶቹ በሚጠይቁት ፍጥነት፣ መጠን፣ ስፋትና ድግግሞሽ ለመስራት አላስቻለውም። በሌሎችም አካባቢዎችና ሁኔታዎች ላይ እንደሚታየው ሁሉ እዚህም ተጎጂዎችና ቤተሰቦች እንዲሁም ምስክሮች በከፍተኛ ፍርሀት ውስጥ መሆንና በሚፈለገው መጠን ትብብር አለማድረጋቸው በዚህ የምርመራ ስራ ሂደት ወቅት ትልቅ ተግዳሮት ፈጥሯል። በመሆኑም ወደፊትም የቀሩ ነገሮች ሊኖሩ ስለሚችሉ ሰፊና ዝርዝር ጥናት ለማድረግ እንዲችል ሰመጉ ተጎጂዎችና ዜጎችን ጨምሮ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ትብብር እንዲያደርጉለት በዚህ አጋጣሚ በድጋሚ ይጠይቃል።

በደ/ብ/ብ/ህ/ክልል በጌዴኦ ዞን ከመስከረም 27-28 ቀን 2009 ዓ.ም የተፈጸመውን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ በበኩላቸው ያለውን መረጃና ምላሽ እንዲሰጡን በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ለአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮማንድ ፖስት ጽ/ቤት፣ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት፣ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ምክር ቤት፣ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ብሔረሰቦች ም/ቤት፣ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ፖሊስ ኮሚሽን፣ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጸጥታና አስተዳደር ቢሮ ጥር 29 ቀን 2009 ዓ.ም በቁጥር አዋ/ሰ/3362/09 በጻፈው ደብዳቤ ሰመጉ ቢጠይቅም ምንም አይነት ምላሽ አላገኘም። በተጨማሪም በጌዴኦ ዞን ለሚገኙ መንግሥታዊ ተቋማት ማለትም የጌዴኦ ዞን አስተዳደር፣ የጌዴኦ ዞን ፖሊስ መምሪያ፣ የዲላ ዩኒቨርሲቲ ሪፈራል ሆስፒታል ከመስከረም 27-28 ቀን 2009 ዓ.ም ስለተፈጸመው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ያላቸውን መረጃ እንዲያካፍሉን ነሐሴ 29 ቀን 2009 ዓ.ም በቁጥር ER3/M41/06/17 በተጻፈ ደብዳቤ ጥያቄ አቅርቧል። ከነዚህ አካላት መካከልም የጌዴኦ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤትና የዲላ ዩኒቨርሲቲ ሪፈራል ሆስፒታል አዎንታዊ ምላሽ በደብዳቤ መስጠታቸውን በዚህ አጋጣሚ መግለጽ ተገቢ ይሆናል። እነዚህ የመንግሥት አካላት ሰመጉ በሕግ ለተፈቀደለት ሥራ ዕውቅና ሰጥተውና ሕጉን አክብረው ላሳዩት አበረታች ትብብር ሰመጉ ምሥጋናውን ያቀርባል።

# ክፍል አንድ

## 5. በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በጌዴኦ ዞን በተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ የተፈፀሙ የተለያዩ የመብት ጥሰቶች

### መግቢያ

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ከ56 በላይ የሚሆኑ ብሔር ብሔረሰቦችና የነዚህ ብሔረሰቦች ተወላጅ ያልሆኑ በርካታ ሌሎች ኢትዮጵያውያን የሚኖሩበት ክልል ነው። የጌዴኦ ብሔረሰብ በደቡብ ክልል ከሚገኙ ብሔረሰቦች አንዱ ነው። በጌዴኦ ዞን ውስጥ ከተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች ማለትም ከጌዴኦ፣ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ጉራጌ...ወዘተ የተወጣጡ ህዝቦች በጋራ ተስማምተውና ተዋደው ለበርካታ አመታት በአንድነትና በሰላም ኖረዋል። ይሁንና ጌደኦ በጌዴኦ ዞን መስተዳድር በተለያየ እርከንና አመራር ላይ ባሉ አንዳንድ ኃላፊዎች፣ ካድሬዎች፣ በጥቂት ባለሀብቶችና አክራሪ በሆኑ የብሔረሰቡ ተወላጆች አነሳሽነትና ተባባሪነት፣ የጌዴኦ ብሔረሰብ አባል ባልሆኑ የአካባቢው ኗሪ ዜጎች ላይ ግድያ፣ ማቁሰል፣ ንብረት ማውደምና ማፈናቀል በተደጋጋሚ ሲከሰት ቆይቷል።

እ.ኤ.አ በ2007 ዓ.ም በተደረገው የሕዝብና ቤት ቆጠራ መሠረት የጌዴኦ ዞን ሕዝብ ብዛት 879,749 ነው። ከዚህ ውስጥ የጌዴኦ ብሔረሰብ አባላት ብዛት 740,720 ሲሆን የሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች አባላት 139,209 እንደሚጠጋ እ.ኤ.አ በ2007 ዓ.ም. የተደረገው የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ያረጋግጣል።

የጌዴኦ ዞን ከአዲስ አበባ ከተማ በ410 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ኢትዮጵያ በአለምአቀፍ የቡና ገበያ ካስመዘገበቻቸው የቡና አይነቶች መካከል ዋነኞቹ የሚመረቱበት ዞን ነው። ግጭቱ ወደ ውጪ ገበያ በሚላከው የቡና ምርት ላይ ተጽዕኖ ፈጥሯል።

ከዚህ በፊትም በነዚሁ አካላት አነሳሽነት በጌዴኦ ዞን በፍስህ ገነት፣ በይርጋጨፌ፣ በዲላ፣ በቡሌና በጨለለቅቱ ከተሞች ውስጥ የሚኖሩ ጥቂት የጌዴኦ ብሔረሰብ ተወላጆች በሌሎች ብሔረሰብ ተወላጆች ላይ መጋቢት 28 1998 ዓ.ም. ባደረሱት ጥቃትና በተከተለው ሁከት፣ በሰው ህይወትና ንብረት ላይ የደረሰውን ጉዳት ዝርዝር ኢሰመጉ በ25ኛ መደበኛ መግለጫው አውጥቷል። ኢ/ሰመጉ በዚህ መግለጫው ለግጭቱ መቀስቀስና መባባስ፣ ለደረሰውም ጥፋት ተጠያቂ የሆኑት የመንግሥት ኃላፊዎችና ተባባሪዎች ለህግ እንዲቀርቡ፣ ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች ካሳ እንዲያገኙ፣ አካባቢያቸውን ለቀው የተሰደዱትም ወደ ቀዬአቸው እንዲመለሱ እና ለችግሩም አስቸኳይና የማያዳግም መፍትሄ እንዲፈለግ አሳስቦ ነበር። ይሁን እንጂ መንግስት በድርጊቱ ፈጻሚዎች ላይ፣ የተሟላና የማያዳግም እርምጃ በወቅቱ አልወሰደም ነበር።

ስለሆነም ሰመጉ በዞኑ "ብሔረሰብ ተኮር ጥቃት ከተፈጸመ ከአንድ ዓመት በኋላ በድጋሚ ሚያዝያ 22 ቀን 1999 ዓም ባወጣው 100ኛ ልዩ መግለጫው፣ የክልሉ መንግስት ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት የፈፀሙትን ባለሥልጣናትና ሌሎች ሰዎች ለህግ በማቅረብ በሕገ መንግስቱ የተጣለበትን ግዴታ እንዲወጣ በድጋሚ መጠየቁም ይታወሳል። በዚሁ 100ኛ ልዩ መግለጫውም፣ የጉዳቱ ሰለባ ከሆኑት የአምስቱ ከተሞች ነዋሪ ዜጎች መካከል ለቡሌ ከተማ የጉዳት ሰለባዎች የደቡብ ክልል መንግስት የመልሶ ማቋቋም ስራ መስራቱ በበጎ ተግባርነቱ የሚታይና የሚበረታታም እርምጃ መሆኑን ኢ/ሰመጉ በወቅቱ ገልጾ ነበር። በተመሣሣይም በቀሪዎቹ አራት ከተሞችም የጥቃቱ ሰለባ ለሆኑ ተጎጂዎች፣ የክልሉ መንግሥት በቂ የመልሶ ማቋቋም ትኩረት እንዲሰጥ ሰመጉ ጥሪውን በድጋሚ አስተላልፎ ነበር። ነገር ግን ከፍተኛ ሰብዓዊና ቁሳዊ፣ የስነልቦናና የሞራል ጥፋትም ያደረሱት ሰዎችም ለህግ አለመቅረባቸው፣ ተጎጂዎችም ፍትሕ አለማግኘታቸው መሰረታዊ የፍትህ መጓደል ከመሆኑም በተጨማሪ የጥቃቱ ሰለባ የሆኑ በርካታ ዜጎች የወደፊት ህይወታቸውን በሰላም ለመምራት እንዳልቻሉ፣ ዋስትና እንዳጡና በከፍተኛ ስጋት ውስጥ እንደሚገኙ ለሰመጉ በወቅቱ ማመልከታቸው በ100ኛ ልዩ መግለጫው ላይ ተገልጿል።

የደቡብ ክልል መስተዳድርም ሆነ የፌዴራል መንግስት በነዚህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ፈጻሚዎች ላይ ከአድልዎ የጸዳ፣ ፈጣን፣ የማያዳግምና ሁሉን አቀፍ የሕግና የአስተዳደር እርምጃ ባለመውሰዳቸውና ተገቢ ማስተካከያም ባለማድረጋቸው ብሔረሰብ-ተኮር ጥቃቱ በመባባስና በዜጎች ህይወትና ንብረትና የኑሮ ዋስትና ላይ አሁንም ከፍተኛ ጥፋትና ጉዳት በማድረስ ላይ ይገኛል። ይህም በሚያሳዝን መልኩ የሚያሳየው ከ10 ዓመት በኋላም ትምህርት አለመወሰዱንና ተመሳሳይና ተደጋጋሚ ጥፋቶችን መከላከልና ማስቆም አለመቻሉን ነው።

በየጊዜው በተለያየ መልክ የቀጠሉት አነስተኛና ጥቃቶችና ማሸማቀቆች ሳይቆጠሩ፣ አሁን ከ10 ዓመት በኋላም በጌዴኦ ዞን በመስከረም 27 እና 28 2009 ዓ.ም በሁለት ቀናት ውስጥ "የተደራጁ ጥቂት የጌዴኦ ብሔረሰብ አባላት ከ (ጌዴኦ) ዞን አመራር እስከ ቀበሌ ህዋስ ያሉትን የመንግስት መዋቅሮች በመጠቀምና የጌዴኦ ብሔረሰብ አባላት በሆኑ የፖሊስ አባላት ተባባሪነት፤ ከጌዴኦ ብሔረሰብ አባላት ውጭ በሆኑ ዜጎች ላይ ከላይ በተጠቀሱት ቀናት ባደረሱት ጥቃት የበርካታ ዜጎች ህይወት ጠፍቷል፣ የአካል ጉዳት ደርሷል፣ በብዙ መቶ ሚሊዮን ገንዘብ የሚገመት ንብረት ተዘርፏል፣ የመኖሪያና የንግድ ድርጅቶች እንዲሁም ተሽከርካሪዎች እና የቡና መፈልፈያ ኢንዱስትሪዎችን በእሳት አውድመዋል" ሲሉ የጥቃቱ ሰለባዎች ለሰመጉ አመልክተዋል።

ከላይ በተጠቀሱት ቀናት ውስጥ በርካታ ሰዎች መሞታቸውንና መቁሰላቸውን፣ ከ90 በላይ ቀላልና ከባድ ተሽከርካሪዎች፣ ከ4 በላይ ወፍጮዎችና የቡና መፈልፈያ ማሽኖች፣ በርካታ የመኖሪያ እና የንግድ ቤቶች መቃጠላቸውን፣ 2540 ሰዎች መታሰራቸውን የጌዴኦ ብሔረሰብ ተወላጅ የሆኑ የሀገር ሽማግሌዎች ገልፀው በደረሰው ጥፋት ማዘናቸውን ጉዳዩን ለማጣራት በአካባቢው ለተገኙት የሰመጉ ባለሙያዎች አስረድተዋል። የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንም (ኢቢሲ) በግጭቱ በርካታ ሰዎች መሞታቸውንና በርካታ ንብረት መውደሙን በጊዜው መዘገቡም ይታወሳል።

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

## 5.1 በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት (ሕገ ወጥ ግድያ)

***ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ*** አንቀጽ 3 "እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት" እንዳለው ያረጋግጣል። ኢትዮጵያ ፊርማ የተቀበለችው ***የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳንም*** በአንቀጽ 6 (1) እና 9 (1) ላይ ይህንኑ መብት በማረጋገጥ፣ መንግሥታት በቃል ኪዳኑ የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸውም በአንቀጽ 2(1) እና 2(2) ይደነግጋል። ***የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር*** አንቀጽ 4 "ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደህንነት ሊከበርለትና ሊጠበቅለት ይገባል። ማንም እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ ሊነፍገው አይገባም" ይላል። ***የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት*** አንቀጽ 14 "ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው" ሲል ይደነግጋል። ኢትዮጵያም እነዚህን አለም ዓቀፍ እና አህጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች የተቀበለች ሀገር እንደመሆኗ ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ ተጥሎባታል።

ይሁን እንጂ እነዚህን ሕገ መንግሥታዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት በጌድኦ ዞን በሚገኙ ከተሞች ነዋሪ ለነበሩ ዜጎች መንግስት በቂ ጥበቃ ባለማድረጉ በሚከተሉት ዜጎች ላይ ግድያ ተፈጽሟል።

1. **ወጣት ፋኑኤል ባዩ** እድሜው 30 ሲሆን በጌድኦ ዞን በዲላ ዙሪያ ወረዳ ጎላ ቀበሌ ነዋሪ ነበር። ወጣት ፋኑኤል ታሞ በመኖሪያ ቤቱ ተኝቶ እንዳለ መስከረም 28 ቀን 2009 ዓ.ም በጌድኦ ማህበረሰብ አባላት እንደተገደለና ቤቱም እንደተቃጠለ ምስክሮች ለሰመጉ ገልጸዋል። የቀብር ስነ ስርዓቱም መስከረም 29 ቀን 2009 ዓም በዳማ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ተፈፅሟል።

2. **አቶ አህመድ በላይነህ** እድሜያቸው 65 ሲሆን ዲላ ከተማ ሀራ ወላቦ ክፍለ ከተማ ሀሴዴላ ቀበሌ መንደር ክልል ውስጥ ነዋሪ ነበሩ። መስከረም 28 ቀን 2009 ዓም ከጠዋቱ 3 ሰዓት በጥቂት የጌድኦ ብሔረሰብ ተወላጆች በገጀራና በዱላ ተደብድበው እንደገደተገደሉ የአይን እማኞች ለሰመጉ ገልጸዋል። የቀብር ስነስርዓቱም መስከረም 29 ቀን 2009 ዓ.ም ዲላ ከተማ በሚገኘው የሙስሊሞች መቃብር ተፈፅሟል።



3. **አቶ ከድር ጉራቾ** እድሜያቸው 60 ሲሆን በመካኒክነት ሙያ የሚተዳደሩና የአካል ጉዳተኛ ነበሩ። መስከረም 28 ቀን 2009 ዓ.ም ከጠዋቱ 4 ሰዓት ቁጥራቸው ከ200 በላይ የሚሆኑ የጌድኦ ብሔረሰብ ዓባላት ዲላ ከተማ አስዴላ ቀበሌ በመኖሪያ ግቢያቸው ውስጥ እንዳሉ በፌሮ ብረት ጭንቅላታቸውንና እግራቸውን ተመተው ህይወታቸው አልፏል። የቀብር ስነ ስርዓታቸውም መስከረም 30 ቀን 2009 ዓ.ም ዲላ ከተማ በሚገኘው የሙስሊሞች መቃብር ተፈፅሟል።



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

4. **አቶ ቶሎሳ ዘለቀ** ዕድሜው 53 በንግድ ስራ የሚተዳደሩ የነበረ ሲሆን መስከረም 27 ቀን 2009 ዓ.ም ከምሽቱ 12 ሰዓት ፍስሀ ገነት 01 ቀበሌ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ እንዳሉ 50 የሚሆኑ የጌድኦ ተወላጆች የግቢያቸውን በር ሰብረው ገብተው በገጀራ ደጋግመው ከመቷቸው በኋላ አንገታቸውን በስለት በመውጋት እንደተገደሉ የሟች ቤተሰቦችና ምስክሮቻቸው ለሰመጉ አረጋግጠዋል፡፡ የቀብር ስነ ስርዓታቸውም መስከረም 29 ቀን 2009 ዓ.ም በፍስሀ ገነት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስትያን ተፈፅሟል፡፡



5. **ወጣት አቡሽ ተስፋዬ** ዕድሜው 25 ሲሆን በጎሚስታ ስራ የሚተዳደር ወጣት ነበር፡፡ መስከረም 28 ቀን 2009 ዓ.ም ከረፋዱ 5 ሰዓት አካባቢ ይርጋጨፌ ከተማ ውስጥ በፖሊሶች በጥይት አንገቱንና ሆዱ ላይ ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል፡፡ የቀብር ስነ ስርዓቱም መስከረም 29 ቀን 2009 ዓ.ም ይርጋጨፌ ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን መፈጸሙን ምስክሮች ለሰመጉ ገልጸዋል፡፡



6. **ወጣት ብርሀኔ ሰለሞን** እድሜ 20 የነበረ ሲሆን መስከረም 28 ቀን 2009 ዓ.ም. ከረፋዱ 5 ሰዓት አካባቢ ይርጋጨፌ ከተማ ከፌደራል ፖሊስ በተተኮሰ ጥይት ተገድሏል፡፡ የቀብር ስነ ስርዓቱም መስከረም 29 ቀን 2009 ዓ.ም ይርጋጨፌ ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን መፈጸሙን ምስክሮች ለሰመጉ ገልጸዋል፡፡



7. **ወጣት መቻል እንዳለ** ዕድሜው 16 ሲሆን ይርጋጨፌ ከተማ መስከረም 27 ቀን 2009 ዓ.ም ከምሽቱ 12 ሰዓት ከ200 በላይ የሚሆኑ የጌድኦ ተወላጆች መጤ ይውጣ በማለት እየተኮሱ ባሉበት ወቅት በጥይት ሆዱን ተመትቶ ሕይወቱ ማለፉን የአይን እማኞች ለሰመጉ ገልጸል፡፡ የቀብር ስነ ስርዓቱም መስከረም 28 ቀን 2009 ዓ.ም ይርጋጨፌ ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን ተፈፅሟል፡፡
8. **ወጣት ቴዎድሮስ ሀጎስ** ዕድሜው 21 ሲሆን መስከረም 28 ቀን 2009 ዓ.ም ከረፋዱ አምስት ሰዓት አካባቢ ይርጋጨፌ ከተማ በጌድኦ ማህበረሰብ አባላት መገደሉን ምስክሮች ለሰመጉ ገልጸዋል፡፡ የቀብር ስነ ስርዓቱም መስከረም 29 ቀን 2009 ዓ.ም በይርጋጨፌ ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን ተፈፅሟል፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት ሰመጉ በመስክ ምርመራ ካረጋገጠው የሟቾች ስም ዝርዝር በተጨማሪ የዲላ ዩኒቨርሲቲ የጤናና የህክምና ሳይንስ ኮሌጅና ሪፈራል ሆስፒታልን ከመስከረም 27-28 ቀን 2009 ዓ.ም በጌዴኦ ዞን በዲላ ከተማና በተለያዩ አካባቢዎች በተፈጠረው ጥቃትና ግጭት ህይወታቸውን ያጡ ሰዎች ዝርዝር እንዲገለጽለትና



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

እንዲሰጠው በደብዳቤ ጠይቋል።በዚህም መሠረት ሆስፒታሉ 4 ገጽ አባሪ የተደረገበትን ዝርዝር ጳጉሜ 1 ቀን 2009 ዓ.ም በቁ/4/218/1149/1 በተጻፈ ደብዳቤ ለሰመጉ በመስጠት ሃላፊነቱን ተወጥቷል።

ሰንጠረዥ 3፡ በደቡብ ክልል በጌዴኦ ዞን ተከስቶ በነበረው ጥቃትና ግጭት ህይወታቸውን ያጡ ዜጎች ስም ዝርዝር (ከዲላ ሪፈራል ሆስፒታል የተገኘ ማስረጃ)

| ተ.ቁ | የሟች ስም | የካርድ ቁጥር | እድሜ | ጾታ | ወረዳ | የጉዳቱ አይነት | ሆ/ል የገባበት ቀን | የሞተበት ቀን | የሞት ምክንያት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ህይወት ታደሰ | 002297/09 | 15 | ሴ | ዲላ | በጥይት ተመታ | 28/1/09 | 29/1/09 | የጭንቅላት ጉዳት |
| 2 | ኑሩ ከድር | 002321/09 | 25 | ወ | ›› | በስለት ተወግቶ | | 28/1/09 | ›› |
| 3[2] | ፋኑኤል ባዩ | 002340/09 | 30 | ወ | ዲላ ዙሪያ | ›› | | ›› | ›› |
| 4 | ዱሎ ሳንኪ | 002236/09 | 45 | ወ | ›› | በጥይት ተመቶ | | ›› | ከፍተኛ የደም መፍሰስ |
| 5 | ጌታቸው ተሰማ | 002305/09 | 15 | ወ | ›› | በስለት ተወግቶ | | ›› | የጭንቅላት ጉዳት |
| 6 | ደረጀ ተፈራ | 002338/09 | 15 | ወ | ›› | በብረት ተመቶ | | ›› | ›› |
| 7 | አቡሽ ፈይሳ | 002314/09 | 14 | ወ | ›› | በብረት ተመቶ | | ›› | ›› |
| 8 | ከበደ ሳሊ | 002233/09 | 20 | ወ | | በጥይት ተመቶ | 28/1/09 | 30/1/09 | ከፍተኛ የደም መፍሰስ |
| 9 | እንደገና ፊሳ | 002254/09 | 20 | ወ | ዲላ | ›› | ›› | 28/1/09 | ›› |
| 10[3] | ከድር ጉራቻ | 002304/09 | 60 | ወ | ›› | በስለት ተወግቶ | | ›› | ›› |
| 11 | ገነነ ሺፈራው | 002226/09 | 15 | ወ | ወናጎ | በጥይት ተመቶ | 28/1/09 | 6/02/09 | ከፍተኛ የደም መፍሰስ፣ ኢንፌክሽን |
| 12 | ሀብታሙ ደጉ | 002193/09 | 50 | ወ | ዲላ | ›› | | 28/1/09 | ከፍተኛ የደም መፍሰስ |
| 13 | ቦጋለ መንገሻ | 002180/09 | 30 | ወ | ዲላ ዙሪያ | ›› | 27/1/09 | 04/2/09 | |
| 14 | ጋሹ ጂቦ | 002230/09 | 25 | ወ | ›› | ›› | 28/1/09 | 29/1/09 | |
| 15 | ደመቀ ዋለልኝ | 002161/09 | 28 | ወ | ዲላ | ›› | ›› | 28/1/09 | ከፍተኛ የደም መፍሰስ |
| 16 | ነብዩ ተሰማ | 002306/09 | 32 | ወ | ዳራ | ›› | | ›› | ›› |
| 17 | ጴጥሮስ ሽጉጤ | | 30 | ወ | | በእሳት ተቃጥሎ | | ›› | የመተንፈሻ አካላት ጉዳት |
| 18 | ገሰሰ ተሸመ | | 30 | ወ | ዲላ ዙሪያ | በስለት ተወግቶ | | ›› | ከፍተኛ የደም መፍሰስ |
| 19 | ማንነታቸው [4] ያልታወቀ | | | ወ | | ›› | | 28/1/09 | |
| 20 | ማንነታቸው [5] ያልታወቀ | | | ወ | | በብረት ተመቶ | | 28/1/09 | |
| 21 | ጲጋዬ መንገሻ | | 25 | ወ | ዲላ | በጥይት ተመቶ | 28/1/09 | 01/2/09 | ከፍተኛ የደም መፍሰስ |
| 22 | ዘመድኩን ደመቀ | | 18 | ወ | ›› | ›› | | 28/1/09 | |
| 23 | ወርቅነህ አለማየሁ | | | ወ | | ›› | | ›› | |

## 5.2 የአካል ጉዳት

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3 "እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት" እንዳለው ያረጋግጣል። ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳንም በአንቀጽ 6 (1) እና 9 (1) ላይ ይህንኑ መብት በማረጋገጥ፣ መንግሥታት በቃል ኪዳኑ የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸዉ የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸውም አንቀጽ 2(1) እና (2) ይደነግጋል። የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 4 "ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደህንነት ሊከበርለትና ሊጠበቅለት ይገባል። ማንም እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ

[2] በተራ ቁጥር 3 የተጠቀሰው በሰመጉ የምርመራ ወቅት የተገኘ ነው።

[3] በተራ ቁጥር 10 የተጠቀሰው በሰመጉ የምርመራ ወቅት የተገኘ ነው።

[4] በተራ ቁጥር 19 ላይ የተገለጸው ግለሰብ ማንነቱ የማይታወቅ ቢሆንም በግጭቱ ምክንያት መሞቱን ከዲላ ሪፈራል ሆስፒታል የተገኘው ማስረጃ ያመለክታል።

[5] በተራ ቁጥር 20 ላይ የተገለጸው ግለሰብ ማንነቱ የማይታወቅ ቢሆንም በግጭቱ ምክንያት መሞቱን ከዲላ ሪፈራል ሆስፒታል የተገኘው ማስረጃ ያመለክታል።



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

ሊነፍገው አይገባም" ይላል። የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 14 "ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው" ሲል ይደነግጋል። እነዚህን ስምምነቶችና በህግ የተደነገገውን በመጣስ ከዚህ በታች ስማቸው በተጠቀሱት ዜጎች ላይ ድብደባና ማሠቃየት ተፈጽሟል።

ሰንጠረዥ 4: ከመስከረም 27-28 ቀን 2009 ዓ.ም በጌዴኦ ዞን በዲላ ከተማና በተለያዩ አካባቢዎች በተፈጸመው ጥቃትና ግጭት የቆሰሉ ሰዎች ዝርዝር (ከዲላ ዩኒቨርሲቲ ጤናና ህ/ክምና ሳይንስ ኮሌጅና ሪፈራል ሆስፒታል የተገኘ ማስረጃ):

| ተ.ቁ | የተጎጂው ስም | የካርድ ቁጥር | እድሜ | ጾታ | ወረዳ | ቀበሌ | የጉዳቱ አይነት | ከሆ/ል የወጣበት ቀን | የጉዳቱ መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲሱ ተሰማ | 002211/09 | 18 | ወ | ዲላ | - | በብረት ተመትቶ | 28/1/09 | ቀላል |
| 2 | ውቡ ንብረት | 002383/09 | 42 | ›› | ›› | 02 | ›› | 01/2/09 | ›› |
| 3 | መልካሙ በቀለ | 002202/09 | 18 | ›› | ›› | - | ›› | 28/1/09 | ›› |
| 4 | አያሌው ሙስጠፋ | 002183/09 | 21 | ›› | ›› | 02 | በድንጋይ ተመትቶ | 27/1/09 | ›› |
| 5 | ሀብታሙ ተሰማ | 002172/09 | 19 | ›› | ›› | 08 | ›› | ›› | ›› |
| 6 | ፍቅረም አለሙ | 002121/09 | 26 | ›› | ›› | 02 | ›› | ›› | ›› |
| 7 | ትንሳኤ ሀይሉ | 002142/09 | 20 | ሴ | ›› | ሀርሱ | በብረት ተመትቶ | ›› | ›› |
| 8 | አዱኛ ጠበቆ | 002164/09 | 22 | ወ | ዲላ ዙሪያ | ቱምቲቻ | ›› | ›› | ›› |
| 9 | እስራኤል ሽፈራው | 002347/09 | 20 | ወ | ገደብ | - | ›› | 29/1/09 | ›› |
| 10 | ታሪካየሁ ሀይሉ | 002170/09 | 13 | ወ | ዲላ | ሀርሱ | ›› | 27/1/09 | ›› |
| 11 | ሳራ ሳሙኤል | 002486/09 | 13 | ሴ | ›› | 08 | ›› | 03/2/09 | ›› |
| 12 | ዘርአየሁ ሽብሩ | 002469/09 | 38 | ወ | ›› | 04 | ›› | 02/2/09 | ›› |
| 13 | ውባለም መሳይ | 002417/09 | 19 | ሴ | ›› | 01 | ›› | 01/2/09 | ›› |
| 14 | ደሳለኝ ይመር | 002156/09 | 35 | ወ | ›› | - | ›› | 27/1/09 | ›› |
| 15 | ወርቅነሽ ገዳ | 002372/09 | 40 | ሴ | ዲላ ዙሪያ | ማችሳስስታ | | 30/1/09 | ›› |
| 16 | አስቴር ታደሰ | 002237/09 | 40 | ›› | ሲዳማ | ቀባዳ | | 28/1/09 | ›› |
| 17 | አብዩት ዮሃንስ | 002209/09 | 24 | ወ | ዲላ | - | በብረት ተመትቶ | ›› | ›› |
| 18[6] | ማንነቱ ያልታወቀ | 002248/09 | 22 | ›› | ›› | - | ›› | ›› | ›› |
| 19 | ግርማ አበበ | 002337/09 | 23 | ›› | ›› | ሀሴዲላ | ›› | 29/1/09 | ›› |
| 20 | ሙሉጌታ በቀለ | 002148/09 | 24 | ›› | ›› | 06 | ›› | 28/1/09 | ›› |
| 21 | ዳዊት ሙሉጌታ | 002217/09 | 25 | ›› | ›› | - | ›› | ›› | ›› |
| 22 | ፀጋዬ ወራሳ | 002470/09 | 46 | ›› | ›› | 04 | ›› | 02/2/09 | ›› |
| 23 | ተስፋዬ ሌጌ | 002240/09 | 50 | ›› | ›› | - | ›› | 28/1/09 | ›› |
| 24 | ሙላቱ ሽፈራው | 002280/09 | 16 | ›› | ›› | - | ›› | ›› | ›› |
| 25 | በፍቃዱ ገ/ህወት | 002227/09 | 10 | ›. | ›› | - | ›› | ›› | ›› |
| 26 | መስፍን ምጽላል | 002193/09 | 65 | ›› | ›› | - | ›› | ›› | ›› |
| 27 | ደሳለኝ እንደሻው | 002194/09 | 26 | ›› | ዲላ ዙሪያ | - | ›› | ›› | ›› |
| 28 | ሐረግ ተመስገን | 002238/09 | 30 | ሴ | ወናጎ | 01 | ›› | ›› | ›› |
| 29 | አብረሀም አለቶ | 002366/09 | 21 | ወ | ዲላ | ሀርሱ | ›› | 30/1/09 | ›› |
| 30 | አብረሀም አለሙ | 002369/09 | 25 | ›› | ›› | ›› | ›› | ›› | ›› |
| 31 | ታምሩ ያብ | 002354/09 | 25 | ›› | ›› | - | ›› | ›› | ›› |
| 32 | ሳሙኤል በየኔ | 002165/09 | 23 | ›› | ›› | 06 | ›› | 27/1/09 | ›› |
| 33 | ተስፋዬ ጎቻ | 002463/09 | 36 | ›› | ›› | 06 | ›› | 02/2/09 | ›› |
| 34 | ፊይሳ ጎሹ | 002319/09 | 35 | ›› | ›› | 08 | ›› | 29/1/09 | ›› |
| 35 | አማኑኤል አራርሶ | 002154/09 | 26 | ›› | ›› | - | ›› | 27/1/09 | ›› |
| 36 | አብነት ታደሰ | 002177/09 | 18 | ›› | ዲላ ዙሪያ | አትቾ | ›› | ›› | ›› |
| 37 | ደሳለኝ ብርሀኑ | 002171/09 | 25 | ›› | ዲላ | - | ›› | ›› | ›› |

[6] በተራ ቁጥር 18 የተገለጸው ግለሰብ ማንነቱ የማይታወቅ ቢሆንም በግጭቱ ምክንያት መሞቱን ከዲላ ሪፈራል ሆስፒታል የተገኘው ማስረጃ ያመለክታል።



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

| ተ.ቁ | የተጎጂው ስም | የካርድ ቁጥር | እድሜ | ጾታ | ወረዳ | ቀበሌ | የጉዳቱ አይነት | ከሆ/ል የወጣበት ቀን | የጉዳቱ መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 38 | ምትኩ በዴሳ | 002244/09 | 18 | ወ | ዲላ ዙሪያ | ጨ.ጩ | ›› | 28/1/09 | ›› |
| 39 | አድዋ ያቴን | 002357/09 | 18 | ›› | ዲላ | - | ›› | 01/2/09 | ›› |
| 40 | አማኑኤል ዳዊቲ | 002149/09 | 16 | ›› | ዲላ ዙሪያ | ጉላ | የአካል መቆረጥ | 27/1/09 | ›› |
| 41 | ክፍያለው ዘነበ | 002346/09 | 25 | ›› | ወናጎ | ዶዶሮ | ›› | 29/1/09 | ›› |
| 42 | ክብሩ ቦጋለ | 002201/09 | 24 | ›› | ዲላ | 08 | በብረት ተመቶ | 28/1/09 | ›› |
| 43 | አቦዬ አጋ | 002148/09 | 25 | ›› | ሀገረሰላም | ጎንፎቻ | በብረት ተመቶ | ›› | ›› |
| 44 | ገመቹ ከድር | 002128/09 | 22 | ›› | ዲላ | ዲላ | በድንጋይተመቶ | 27/1/09 | ›› |
| 45 | ኤፍሬም ዮሃንስ | 002364/09 | 19 | ›› | ወናጎ | ገለቾ | በስለት ተወግቶ | 30/1/09 | ›› |
| 46 | ጌታቸው ጉንትራ | 002423/09 | 24 | ›› | ዲላ | 02 | በብረት ተመቶ | 01/2/09 | ›› |
| 47 | ያሬድ ግርማ | 029733/08 | 25 | ›› | ወናጎ | ወናጎ | ›› | 28/1/09 | ›› |
| 48 | ብርሀኑ ቱጋ | 002426/09 | 27 | ›› | ዲላ | 02 | በድንጋይ ተመቶ | ›› | ›› |
| 49 | አምት መዴ | 023971/09 | 22 | ›› | ›› | 05 | በብረት ተመቶ | 02/1/09 | ›› |
| 50 | ተስፋለም ዘውዴ | 002425/09 | 20 | ›› | ›› | ዲላ ዩኒቨር | ›› | 01/2/09 | ›› |
| 51 | ማንደፍሮ ገመዳ | 002232/09 | 15 | ›› | ›› | ዲላ | በስለት ተወግቶ | 28/1/09 | ›› |
| 52 | ናስር ሁሴን | 002196/09 | 35 | ›› | ›› | 06 | በብረት ተመቶ | ›› | ›› |
| 53 | አዳነ አርፋስ | 002249/09 | 20 | ›› | ›› | ዲላ | ›› | ›› | ›› |
| 54 | ዳንኤል ሽብሩ | 002281/09 | 28 | ›› | ›› | ›› | በድንጋይ ተመቶ | ›› | ›› |
| 55 | አብረሀም ባሊ | 002232/09 | 20 | ›› | ›› | ›› | በብረት ተመቶ | ›› | ›› |
| 56 | ምህረቱ ዘውዴ | 002203/09 | 16 | ›› | ›› | ›› | በስለት ተወግቶ | ›› | ›› |
| 57 | መክብብ ሳሙኤል | 002212/09 | 21 | ›› | ›› | ›› | ›› | ›› | ›› |
| 58 | ትግሌ በኮ | 002200/09 | 26 | ›› | ይርጋጨፌ | 02 | ብረት ተመቶ | ›› | ›› |
| 59 | ፍቃዱ በቀለ | 002274/09 | 22 | ›› | ዲላ | ዲላ | ›› | ›› | ›› |
| 60 | ግዛው ቦንቱ | 002207/09 | 21 | ›› | ›› | ›› | ›› | ›› | ›› |
| 61 | ታዬ ዳቡ | 002242/09 | 24 | ›› | ›› | ›› | በስለት ተወግቶ | ›› | ›› |
| 62 | ተስፋዬ ሽፈራው | 002351/09 | 22 | ›› | ገደብ | ጊደቾ | በድንጋይ ተመቶ | 02/2/09 | ›› |
| 63 | ሙሉነህ ታደሰ | 002353/09 | 17 | ›› | ዲላ | 06 | ›› | 30/1/09 | ›› |
| 64 | ኤፍሬም ተሸመ | 002365/09 | 20 | ›› | ይርጋጨፌ | ኪንጋ | በብረት ተመቶ | 28/1/09 | ›› |
| 65 | ደስታ ባንተ | 002352/09 | 45 | ›› | ዲላ | ዲላ | ›› | 30/1/09 | ›› |
| 66 | አያቤ | 002274/09 | 26 | ›› | ›› | 06 | በድንጋይ ተመቶ | 28/1/09 | ›› |
| 67 | ትዕግስት | 002474/09 | 20 | ሴ | ›› | 08 | በብረት ተመቶ | 02/2/09 | ›› |
| 68 | ታሪኩ | 002199/09 | 30 | ወ | ›› | 08 | ›› | 28/1/09 | ›› |
| 69 | ወንድወሰን አበበ | 002158/09 | 26 | ›› | ›› | 04 | በድንጋይ ተመቶ | 27/1/09 | ›› |
| 70 | በቀለ ብርሀኑ | 002510/09 | 42 | ›› | ›› | ዲላ | በብረት ተመቶ | 03/2/09 | ›› |
| 71 | ዝናሽ ወ/ጊዮርጊስ | 002310/09 | 42 | ሴ | ›› | 07 | ›› | 29/1/09 | ›› |
| 72 | ሰኢድ ቃሲም | 002298/09 | 26 | ወ | ›› | ሀሮሳ | በድንጋይ ተመቶ | ›› | ›› |
| 73 | አብዮት ታደሰ | 002323/09 | 35 | ›› | ዲላ ዙሪያ | ሶሰፋ | በብረት ተመቶ | ›› | ›› |
| 74 | ደሳለኝ ታደሰ | 002159/09 | 18 | ›› | ዲላ ዙሪያ | አሞባ | ›› | ›› | ›› |
| 75 | በዴቻ ሀመሶ | 002144/09 | 38 | ›› | ዲላ | 08 | ›› | 27/1/09 | ›› |
| 76 | አቤ ንጉስ | 002157/09 | 23 | ›› | ›› | - | ›› | ›› | ›› |
| 77 | ባዬ ያዴቻ | 002330/09 | 95 | ›› | ዲላ ዙሪያ | ዲላ | ›› | 29/1/09 | ›› |
| 78 | ማሙሽ ንጉስ | 002151/09 | 20 | ›› | ›› | - | ›› | 27/1/09 | ›› |
| 79 | በረከት ዲጆ | 002267/09 | 32 | ›› | ወናጎ | 01 | ›› | 28/1/09 | ›› |
| 80 | ሚልኪያስ አዱኛ | 002160/09 | 17 | ›› | ዲላ | - | ›› | 27/1//09 | ›› |
| 81 | ዘሪሁን በራሶ | 002405/09 | 30 | ›› | ዲላ ዙሪያ | ጨ.ጩ | ›› | 01/2/09 | ›› |
| 82 | ውዱ ጂአ | 002527/09 | 35 | ›› | ይርጋጨፌ | 01 | ›› | 03/2/09 | ›› |
| 83 | ዘሪሁን ዮሐንስ | 026187/09 | 18 | ›› | ዲላ ዙሪያ | - | ›› | 02/2/09 | ›› |
| 84 | አለማየሁ ሽብሩ | 002504/09 | 25 | ›› | ይርጋጨፌ | ይርጋጨፌ | በድንጋይና በብረት ተመትቶ | 28/1/09 | ›› |
| 85 | ሙሉጌታ ማሩ | 002592/09 | 18 | ›› | ›› | ›› | በስለት ተወግቶ | 04/2/09 | ›› |
| 86 | ዘውዴ አሸናፊ | 002595/09 | 18 | ›› | ›› | ›› | በድንጋይና በብረት ተመትቶ | 28/1/09 | ›› |
| 87 | ኤልያስ አየለ | 002286/09 | 30 | ›› | ዲላ ዙሪያ | አቲልቾ | በስለት ተወግቶ | 27/1/09 | ›› |



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

| ተ.ቁ | የተጎጂው ስም | የካርድ ቁጥር | እድሜ | ጾታ | ወረዳ | ቀበሌ | የጉዳቱ አይነት | ከሆ/ል የወጣበት ቀን | የጉዳቱ መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 88 | ጥላሁን ጃሶ | 002152/09 | 38 | ›› | ዲላ | ዲላ | በብረት ተመትቶ | ›› | ›› |
| 89 | ተፈራ ተስፋዬ | 002223/09 | 32 | ›› | ›› | ›› | ›› | ›› | ›› |
| 90 | መስፍን መለሰ | 002241/09 | 18 | ›› | ›› | - | ›› | 28/1/09 | ›› |
| 91 | በድሉ አብረሀም | 002713/09 | 21 | ›› | ›› | 04 | በድንጋይ ተመትቶ | 27/1/09 | ›› |
| 92 | ይውሉስ ባዴ | 002168/09 | 30 | ›› | ›› | 08 | በብረት ተመትቶ | ›› | ›› |
| 93 | ኤፍሬም በቀለ | 002520/09 | 12 | ›› | ይርጋጨፌ | ይርጋጨፌ | ›› | 04/2/09 | ›› |
| 94 | አብነት በየነ | 002581/099 | 20 | ›› | ›› | ›› | ›› | ›› | ›› |
| 95 | ሀብታሙ ተሰማ | 002473/09 | 19 | ›› | ዲላ | 08 | በድንጋይ ተመትቶ | 27/1/09 | ›› |
| 96 | ከፍያለው | 002346/09 | 25 | ›› | ወናጎ | ደደሮ | በስለት ተወግቶ | 29/1/09 | ›› |
| 97 | አያሌው ሙስጠፋ | 002183/09 | 21 | ›› | ዲላ | 02 | በብረት ተመትቶ | 27/1/09 | ›› |
| 98 | ተስፋዬ ወርቁ | 002583/09 | 22 | ›› | ዲላ ዙሪያ | ጉላ | በድንጋይ ተመትቶ | 04/2/09 | ›› |
| 99 | ማሙሽ ሽብሩ | 002593/09 | 22 | ›› | ይርጋጨፌ | ይርጋጨፌ | በብረት ተመትቶ | ›› | ›› |
| 100 | ዘሪሁን በቀለ | 002585/09 | 15 | ›› | ዲላ ዙሪያ | ጉላ | ›› | ›› | ›› |
| 101 | አብረሀም ከፍያለው | 002280/09 | 18 | ›› | ዲላ | ዲላ | በስለት ተወግቶ | 28/1/09 | ›› |

## 5.3. ንብረት ማውደም

የኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀጽ 40 እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ንብረት የማፍራትና በንብረቱም በነጻነት የመጠቀም፣ እንዲሁም ለሚጠፋበት ንብረትና ማፈናቀል በቂና ተመጣጣኝ ካሳ የማግኘት መብት እንዳለው በግልፅ ደንግጓል። በተጨማሪም ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል መብቶች አለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 11(1) እያንዳንዱ ሰው በቂ ምግብ፣ ልብስና መጠለያን ጨምሮ ለራሱና ለቤተሰቡ በቂ ኑሮ የማግኘት መብት እንዳለውና መንግስት ደግሞ የዚህ መብት የማሟላት ግዴታ እንዳለበት ይህ ቃል ኪዳን ይደነግጋል። ይሁንና ከዚህ ድንጋጌ ተቃራኒ በሆነ መልኩ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የመብት ጥሰቶች በዜጎች ላይ ተፈጽመዋል።

በደ/ብ/ብ/ህ/ክ በጌዴኦ ዞን በኮቸሬና ወናጎ ወረዳዎች የፍስሃገነት፣ የጨለለቅቱ እና የወናጎ ከተማዎች ነዋሪዎቻ የሆኑ አመልካቾች ነሓሴ 9 ቀን 2009 ዓ.ም. ለኢ.ፌ.ድ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት እና ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በጻፉት ማመልከቻ እንደገለጹት "ከመስከረም 27-28 ቀን 2009 ዓ.ም. ከላይ በተጠቀሱት ከተማዎች ላይ በጥቂት የአካባቢው ተወላጆችና ጸረ ሰላም ሀይሎች ምክንያት በተከሰተው የጸጥታ ችግር ለበርካታ አመታት በላባቸው ያፈሩትን ንብረት ማለትም የመኖሪያና የንግድ ቤቶች ከነ ሙሉ ቁሳቁሶች፣ ድርጅቶች ከነሙሉ እቃዎች፣ተሽከርካሪዎች፣ የቡና መፈልፈያ ማሽኖች ወ.ዘ.ተ በእሳት ጋይተው ሙሉ በሙሉ ወድመዋል፣ በበርካታ ሰዎችም ላይ የአካል ጉዳትና የህይወት ህልፈትም አስከትሏል"።

በተጨማሪም አመልካቾች ለሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ ጽፈው ባቀርቡት አቤቱታ ላይ መስከረም 27 ቀን 2009 ዓ.ም. የጌዴኦ ብሔርን በማይወክሉ አንዳንድ የጌዴኦ ብሄረሰብ ተወላጆች፣ ጥቂት የመንግስት ሀይሎች እና የታጠቁ የፖሊስ ሰራዊት አባላት በተደራጀና በተቀነባበረ ሁኔታ ለበርካታ አመታት ሰርተው ያፈሩትን የተለያዩ ንብረቶች በእሳት ማቃጠላቸውን፣ መዝረፋቸውንና ማውደማቸውን እና የደረሰውን ጉዳት የክልሉና የፌደራል ባለስልጣናት ጭምር ቦታው ድረስ በመገኘት መመልከታቸውን ገልጸዋል።

